“በዓለት ንቃቃትና በገደል መሸሸጊያ ያለሽ ርግብ ሆይ ቃልሽ መልካም ፊትሽም ያማረ ነውና መልክሽን አሳዪኝ ድምፅሽንም አሰሚኝ”
መኃልየ መኃልይ ሰሎሞን ምዕ2ቁ14

## <u>የክፉ ቀን ደራሽ</u>

ወለል አደረገችው ሁሉን በር ከፋፍታ
ማንም አያስቆማት የቃናዋን እርካታ
እኔ ኃጥኡ ዘንድ ስትመጣ ለዕርዳታ
አብሳልኝ ልትሄድ የዕንባዬን ጠብታ።
ፍጥረት ይታዘዛል ስለቃሏ ክብር
ይኸው ተገልያለት የእመቤቴ ተአምር
አንቺ ነሽ እያላት ስሟን እያነሳ
የክፉ ቀን ደራሽ ልመና የማትረሳ።
ከቶ እንዴት ልግለፀው የድንግልን ሥራ
ምን ብዬስ ልናገር የትኛውን ላውራ
ለምስክርነት አብቅታኝ ከልላ
ከነጣቂው ዲያብሎስ ታድጋኝ አስጥላ።
ስሟ እየጣፈጠኝ ደግሜ ስጣራ
ንዒ ንዒ ስላት ሲገጥመኝ መከራ
መቼ ዝም አለችኝ መጣችልኝ ፈጥና
ቀና ልታደርገኝ ርህርህተ ልቡና።
የመከራው ዘመን አይሎ በርትቶ
ተስፋ እያስቆረጠኝ በኔ ላይ ተነስቶ
ባዶዬን ሊያስቀረኝ ግፉን ሁሉ አብዝቶ
እባብ ክፉ ጠላት መንገድ ላይ አድብቶ
ድንግል ፈጥና ደርሳ ድምጿን ስታሰማ
ብን ብሎ ጠፋ ልክ እንደ ደመና።
የቅዱሳን ትምክህት የገድላቸው ምዕራፍ
መፅናኛ እናታቸው የጽድቃቸው ደጃፍ
ዳርቻ የሌላት ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ
ባርካ የምትሄድ ናት በሕይወታችን ስታልፍ።
ንዒ ንዒ በሏት የተቸገራችሁ
በፈተና ብዛት የተጨነቃችሁ
መግቢያና መውጫውን ድንግል ታሳያችሁ
እሷ ታውቀዋለች ስሟን ከጠራችሁ
የምስራቅ በር ናት የጸሎት መልሳችሁ
ሰምታ ዝም የማትል ትሁት እናታችሁ።

ከኃይለመስቀል ተስፋዬ
16/07/2004 ዓ/ም(ለንደን)

www.ethiopianorthodox.org